# 2023-2024 የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ
# MCPS Title I - የዲስትሪክት ደረጃ ዕቅድ

## የእኛ እምነት

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Title I፣ ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች በጋራ አብረው ሲሰሩ፣ ልጆች ስኬታማ ይሆናሉ ብሎ ያምናል።
- MCPS የሁሉንም ቤተሰቦች ትብብር እና ተሳትፎ ይደግፋል።
- የልጆቻችን ትምህርት ጉዳይ የጋራ ኃላፊነታችን መሆኑ እምነታችን ነው። ቤተሰቦች በሚሳተፉበት ጊዜ ተማሪዎች የበለጠ ስኬታማ ይሆናሉ ብለን እናምናለን።
- የትምህርት ስርዓቱ፣ እንዲሁም እያንዳንዳቸው ትምህርት ቤቶች፣ የወላጆቻችን/የቤተሰቦቻችን እና የማህበረሰባችን ፍላጎቶች እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ለማሟላት ከተለያዩ የዘር/የብሔረሰቦች ልምዶች፣ ከሚጠበቁ ነገሮች እና እሴቶች ጋር የተጣጣሙ ፕሮግራሞችን እና ልምዶችን ለማበልፀግ ቁርጠኛ ናቸው።
- Title I ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ለወላጅ/ለቤተሰብ ተሳትፎ እና ትብብር ያላቸውን ቁርጠኝነት መግለጽና ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።
- እያደገ የመጣው የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ወላጆች/ቤተሰቦች እና አካል ጉዳተኛ ልጆች በተሳትፎ እና በትብብር ጥረቶች ውስጥ ይካተታሉ።
- ይህ እቅድ ከወላጆች/ከቤተሰቦች ጋር በጋራ የተዘጋጀ እና ከትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ABC፣ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስትራቴጂክ እቅድ ጋር የተጣጣመ ነው።
- በዚህ ዕቅድ ውስጥ፣ 'ወላጅ' / 'parent' የልጆችን ትምህርት አሰጣጥ ለመከታተል/ለመቆጣጠር የሚሳተፉ ወላጆችን፣ ሞግዚቶችን፣ እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት እንደሚያሳትፍ ታሳቢ ያደርጋል።

## የእኛ አሠራር-ሒደት

- Title I የዲስትሪክት ደረጃ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ በአንድነት የተዘጋጀው Title I የቤተሰብ አማካሪ ኮሚቴ (FAC) ሲሆን የ Title I ሰራተኞች እና በ Title I ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የቤተሰብ አባላት ተሳትፈውበታል።
- ይሄ ዕቅድ የታይትል I / Title I መስፈርቶች በዲስትሪክት ደረጃ እንዴት እንደሚተገበሩ በሚመለከት መረጃ ይሰጣል።
- የቤተሰብ ወርክሾፖች፣ የወላጆች ስብሰባዎች፣ እና ሌሎች ዝግጅቶች ቤተሰቦች የግምገማ መረጃዎችን በመጠቀም ግብረመልስ መስጠት የሚያስችሉ እድሎች ናቸው።
- ከግምገማ የተገኘው ግብረመልስ በየአመቱ በስፕሪንግ ወቅት FAC ስብሰባ ላይ ይተነተናል። እቅዱን ለማሻሻል እና የቤተሰብ ተሳትፎን ለማዳበር እድሎችን የመፍጠር ምክሮች ተሰጥተዋል።
- በእያንዳንዱ Title I ት/ቤት የትምህርት ቤት እና የቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ ወይም ንድፍ በማዘጋጀት ተመሳሳይ መስፈርቶችን ያካተተ የትምህርት ተሳትፎ ደረጃን ለመፍጠር ይውላል።
- Title I ትምህርት ቤቶች በየትምህርት ቤታቸው ደረጃ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ እቅዳቸውን በየአመቱ በቤተሰብ ተሳትፎ ኮሚቴ ስብሰባዎቻቸው እና በአመራር ስብሰባዎቻቸው ላይ እየገመገሙ ክለሳ ያደርጋሉ።
- የት/ቤት-ደረጃ ዕቅዱ በእያንዳንዱ መኸር/ፎል ወቅት በጋዜጣዎች፣ በኤሌክትሮኒክ መገናኛዎች፣ እና በቤተሰብ ስብሰባዎች/አውደ ጥናቶች ጨምሮ በተለያዩ በርካታ መንገዶች ይሰራጫል።

ይህ ዓመታዊ Title I የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ዕቅድ በ Title I ድረ-ገጽ ላይ ተለጥፎ በፎል ወቅት ለቤተሰቦች ተሰራጭቷል። እንደ ጋዜጦች፣ ጥሪዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ አይነት የመገናኛ መንገዶች በ MCPS 'ዋና' ቋንቋዎች የሚገኙ ይሆናል።

የትምህርት ቤት-ወላጅ/ቤተሰብ ስምምነት ግቦችን፣ የሚጠበቁ ነገሮችን እና የጋራ ሀላፊነቶችን ምንነት ይገልፃል። ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ፎል ላይ ስምምነት (ኮምፓክት) ያዘጋጃል። ስምምነቶቹ በየአመቱ መኸር/ፎል ወቅት ላይ በወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ላይ ይገመገሙ እና ይፈረማሉ። ስምንንቱ ጥቅም ላይ የሚውለው በቤተሰቦች እና በት/ቤቶች መካከል ለሚደረገው የትብብር ጥረት ለተማሪዎች ትምህርታዊ ስኬት እና ለቤተሰቦቻቸው ደህንነት ነው። ስለ ዲስትሪክት ወላጅ እና ቤተሰብ (District Parent & Family) የሚሰጥ ግብረ መልስ እንቀበላለን

**DECTIRF, Title I**
Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road, Room 204
Rockville 20852 ~240-740-4600

# 2023-2024 የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ
# MCPS Title I - የዲስትሪክት ደረጃ ዕቅድ

**MCPS Title I** በስልጠና እና በሙያ ትምህርት በሚደረግ የአቅም ግንባታ ቤተሰቦችን በመደገፍ ያምናል።

## በልዩ ልዩ የቤተሰብ እንቅስቃሴዎች አቅምን መገንባት

የወላጅ አካዳሚ / **Parent Academy TO GO**፦ የ MCPS “የወላጅ አካዳሚ / Parent Academy TO GO” ለወላጆች በቨርችዋል የሚቀርቡ ተከታታዮች ክፍሎች ሲሆኑ መረጃዎቹም የሚያተኩሩት በልጆቻቸው ትምህርታዊ እና የስሜት ጤናማነት/ደህንነት ላይ ነው። በትምህርት አመቱ ውስጥ በየወሩ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ በተለያዩ ርዕሶች ላይ አውደ ጥናቶች ይሰጣሉ፣ ከነዚህም መካከል ስለ፦

- የስቴት የትምህርት ደረጃዎችን፣ የስቴት እና የአካባቢ ትምህርታዊ ምዘናዎች፣ እና የልጅን እድገት እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል፣
- የልጃቸውን አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ደህንነት እንዲያድግ መደገፍ፤
- የተማሪዎችን ስኬታማነት ለማሻሻል ከትምህርት ባለሙያዎች ጋር መስራት፣ እና ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዲሰሩ መርዳት።

---

የቤተሰብ አውደ ጥናቶች፦ Title I የትምህርት ባለሙያዎች በእያንዳንዱ ት/ቤት ለወላጆች/ለቤተሰቦች እና ለት/ቤት ሰራተኛ አባላት ቁሳቁሶችን/ግብዓቶችን እና ስልጠናዎችን በሚከተሉት ላይ ይሰጣሉ፦

- የ Title I መስፈርቶችን መረዳት
- በቤት እና በት/ቤት መካከል ግንኙነትን፣ ትብብርን፣ እና ተደራሽነትን ማጎልበት
- የልጆቻቸውን የትምህርት እድገት በቤት ውስጥ መደገፍ

---

የትምህርት ቤት ወላጅ/ቤተሰብ ተሳትፎ ሂደቶች፦Title I የትምህርት ባለሙያዎች ት/ቤቶችን እና ቤተሰቦችን የሚደግፉት፦

- ከቤተሰቦች ጋር ውጤታማ ግንኙነት፣ ትብብር እና ተሳትፎን በመፍጠር ላይ ምርጥ ተሞክሮዎችን በሚመለከት በ Title I ት/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ መምህራን ግብዓቶችን በማቅረብ እና በማሰልጠን።
- ስኬታማ በሆነ የወላጅ-መምህር ትብብር ላይ እንዲሳተፉ ለቤተሰቦች ሪሶርሶችን እና ስልጠናዎችን መስጠት.
- ወላጆች/ቤተሰቦች ለመተባበር እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፈንድ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ውሳኔ እንዲወስኑ በየሩብ ዓመቱ በሚያደርጉት ስብሰባዎች ከቤተሰብ ተሳትፎ ኮሚቴዎች ጋር መስራት።

## በሠራተኞች ስልጠና አማካይነት የአቅም ግንባታ

የሰራተኞች ስልጠና፦ የዋናው ፅ/ቤት ሰራተኛ አባላት እና ት/ቤት-መሰረት አድርገው እንደሚሰሩ የሰራተኛ አባላት በመሆናቸው በተለያዩ መድረኮች እና ከስራቸው ጋር ተዛማጅ በሆኑ በተለያዩ ርዕሶች ላይ አመቱን በሙሉየቴክኒክ ድጋፎችን በ Title I የትምህርት ባለሙያዎች ይሰጣቸዋል። ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ድጋፍ የሚከተሉትን ያጠቃልላል ነገር ግን በዚህ አይወሰንም፦

- የትምህርት ቤት-ወላጅ/ቤተሰብ የታመቀ እና በት/ቤት ደረጃ የቤተሰብ እና የወላጅ ተሳትፎ እቅድ ማዘጋጀት.
- የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከወላጆች/ቤተሰቦች ጋር እኩል አጋሮች እና ተባባሪዎች ሆነው እንዲሰሩ ሙያዊ ትምህርት ማቀድ እና ማዳበር
- በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እንደ እኩል አጋሮች ከቤተሰቦች ጋር መገናኘት እና መተባበር.
- ከቤተሰብ ተሳትፎ ባለሙያ ጋር በትምህርት ቤት ደረጃ ለወላጆች-ማህበረሰብ አስተባባሪዎች ስልጠና መስጠት።
- የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎን ለማዳበር በትምህርት ቤት ደረጃ የወላጅ-ማህበረሰብ አስተባባሪዎችን ከሪሶርሶች እና ከማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ጋር ማገናኘት።

---

የትምህርት ባለሙያ ሥልጠና፦የ Title I የትምህርት ባለሙያዎች የፌደራል እና የስቴት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ግንኙነት ያደርጋሉ፣ ያስተባብራሉ እና በትብብር ይሰራሉ።Title I ሰራተኞቻቸው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ከት/ቤት ሰራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር በሚጋሩባቸው ጉዳዮች ላይ ስልጠና ያገኛሉ፡-

- ለወላጆች እና ለቤተሰብ ተሳትፎ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ስልቶች/ስትራቴጂዎች
- ዝግጅት፣ ስልጠና፣ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ባጀት ቁጥጥር
- በቤተሰብ ተሳትፎ የበጀት ውሳኔዎች ላይ የወላጆች/ቤተሰቦች ትብብርን ማጎልበት
- Title I ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለቤተሰብ ተሳትፎ ተነሳሽነት እና ጥረቶች ከፌደራል የሚመደብ ባጀት በአግባቡ መጠቀም

## ትምህርት ቤቶችን መርዳት

የልጆች እና የታይትል/Title I ፕሮግራሞች ክፍል እና የተሐድሶ ፈንድ ዲቪዝዮን (DECTIRF) የቤተሰብ ተሳትፎ ተነሳሽነትን በሚመለከት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች ጋር ይገናኛል፣ያስተባብራል እና ይተባበራል።

- ዓመቱን ሙሉ በተለያዩ ኮሚቴዎች ላይ በንቃት ይሳተፋል።
- ለታይትል/Title I ወላጆች/ቤተሰቦች የማዳረስ እና የስልጠና ጥረቶችን ለመደገፍ ከተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ (OSFSE) እና የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች ጋር መገናኘት እና ማቀድ።
- ከቅድመ መዋለ ህጻናት/ሄድ ስታርት ጋር በመተባበር የቤተሰብ ተሳትፎን ለማዳበር የተሳለጠ አካሄድን ለማረጋገጥ ታይትል/Title I ወላጆች/ቤተሰቦች የሥልጠና ጥረቶችን ማቀናጀት።

## ትምህርት ቤቶችን ማስተባበር

Title I የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ጥረቶች እና የቴክኒክ ድጋፍ ለ Title I ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ከ DECTIRF በሚመጡ የ Title I ትምህርት ስፔሻሊስቶች ነው። ታይትል/Title I የማስተማር ባለሙያ ስፔሻሊስቶች የሚሰጡት፦

- ውጤታማ የቤተሰብ ተሳትፎ ተሞክሮዎችን በማቀድ እና በመተግበር የተማሪን ውጤት እና የት/ቤት አፈጻጸምን ለማሻሻል ለት/ቤት ሰራተኞች ድጋፍ፣ መመሪያ እና እገዛ ማድረግ።
- የትምህርት ቤት-ወላጅ/ቤተሰብ ኮምፓክት፣ የት/ቤት-ደረጃ እቅድ እና ሌሎች የወላጅ/ቤተሰብ ተሳትፎ እድሎችን ለማዳበር እገዛ ማድረግ።
- Title I፣ ክፍል A የፌዴራል እና የስቴት መስፈርቶችን መሟላቱን የሚያሳይ እና DECTIRF ላይ የሚቀመጡ ሰነዶች።